# “ውሸትና ስንቅ እያደረ ይቀላል”!!!

ከባህልቢ ዘማርያም

ክፍል ሶስት፤

በክፍል ሁለት የተቋጨው የሐጎስ ዮሐንስን ፅሑፍ መተቸት በመጀመር ነበር። እነሆ! ትችቱ ይቀጥላል።

በሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ በመጀመርያ ገጽ መጀመርያ ፓረግራፍ ውስጥ እንዲህ የሚል ሰፍሮ ይገኛል፤

> *“ዋናው የጥርጣሬ ምክንያት ልጽፍበት ያሰብኩት ርእሰ ጉዳይ አስፈላጊነት ላይ ካለኝ ማወላወል የሚመነጭ ሳይሆን፤ ዋናው በተለይ በኛ በኢሮቦች መሀከል፤ እንዲሁም ባጠቃላይ ሌሎች የሚመለከታቸው ወገኖችና ኢሮቦች መካከል ጥርጣሬና አለመተማመንን እንዳይፈጠር ከመስጋት ነው።”*

ይህ አባባል አንድ በኢሮብ ውስጥ በትክክል ተፈጸመ የሚባለው አነጋገር ያስታውሰናል። በቀጥታ ወደ ነጥቡ ከመግባታችን በፊት ከዚህ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ስላለው የኢሮብ ህዝብ የቆየ አስተዳደር ትንሽ ማለቱ ተገቢ ይሆናል። ኢሮብ የራሱ ባህልና የአስተዳደር ሥርዓት ነበረው። በየጊዜው አስተዳዳሪውን በራሱ ይመርጥና እና የሚል መዓርግ በመስጠት የተወሰነለት የጊዜ ገደብ እስኪጨርስ ድረስ ህብረተሰቡን ያገለግላል፤ ይዳኛል። የተዋጣለት ዴሞክራሲያዊ አሠራር ነበረው ባይባልም፤ ያ ወግና ባህል እንዲወገድ ያደረጉ በተከታታይ አገሪቷን የገዙ ኢ-ዲሞክራሲያዊ መንግሥታት ካመጡብን ጣጣ ጋር ሲነጻጸር ግን እጅጉን የተሻለ እንደነበረ ይወሳል። በዛን ጊዜ የነበሩ አባቶቻችንና እናቶቻችን በጊዜአቸው ማድረግ የሚገባቸውና ሕልናቸው የሚፈቅደውን አድርጓል። ይህ ማለት ግን ይህ ፀሐፊ በዛን ጊዜ የነበረው ሁሉ እንከን የለሽ የተዋጣለት ነበር ለማለት እንዳልሆነ፤ አንባቢ እንዲገነዘብለት ይፈልጋል። አባት እናቶቻችን በኖሩበት ጊዜ ኮሚኒስቶች ወይም ሊበራል ዴሞክራቶች እንዲሆኑ የሚጠብቃቸው ካለ እርሱ ራሱ ጅላጅል ይሆናል። ዋናው ለማነጻጸር የተፈለገው፤ ከነሱ በኋላ የመጡት አገዛዞች እሱን የምንመርጥበትና እሱን እንድንናፍቅ የሚያደርጉን ደንቃራዎች እንደፈጠሩብን ለማሳየት ነው። በአባቶቻችን ጊዜ የሰው ልጅ ሕይወት እንደዛሬ ዋጋ ቢስ አልነበረም። አንድ ሰው ስተሾመ የሰው ልጆችን እንደ እንስሳ እንደፈለገ ማሰርና መግደል በዛን ጊዜ አልነበረም። በደርግና ሕወሓት አገዛዝ ዘመን ህዝባችን ያለፈባቸውና እያለፈባቸው ያለ መከራና ስቃይ በዛን ወቅት የሚታሰብ አልነበረም። በዛን ጊዜ የኢሮብ ሰው የሆነ ሕመም ወይም ሌላ አደጋ ካላጋጠመው ከዋለበት ወደ ቤቱ በሰላም እንደሚመለስ በመተማመን ነበር የሚወጣው። ዛሬ ዛሬ፤ እሱ ነገር ጭራሹን ተረስቶ ሰው በሰላም ወደ ቤቴ እመለስ ይሆን? እያለ ከቤቱ የሚወጣበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። የመኖርና ያለመኖር ዋስትናው በካድሬ እጅ ተጠቃልሎ የገባበት ወቅት ሆኗል። የሆነ ሆኖ እግረ-መንገድ የእና አሰያየም ስለተነሳ እንጂ የዚህ መጣጥፍ የዛሬ ትኩረት አይደለምና ወደ ተነሳንበት እንመለስ። እና! የሐጎስ ዮሐንስ አባባል በአንድ ወቅት እና ገብራይ ተሹመው ለስብሰባ ሕዝብ ማኽል ተቀምጠው በመዳኘት ላይ እያሉ ያጋጠመ ገጠመኝን ነው ለማውሳት የተፈለገው። አንድ ተማሪ ከሩቅ መንደር እየተመላለሰ በዓሊተና ልደታ ት/ቤት ይማር ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን እንደወትሮው ምሳውን በሻንጣው ቋጥሮ ይመጣል። እንጀራውን አስቀምጦ ዞር ሲል ሁለት ብልጦች ካስቀመጠበት ቦታ አንስተው ይበሉበታል። ተመልሶ ሲያይ ያስቀመጠው ምሳ ያስቀመጠበት ቦታ ላይ እንደሌለ

ይገነዘባል። በዚህም ብልጦቹን ለምሳ ያመጣው እንጀራ አንስተው እንደሆነ ይጠይቃቸዋል። በዕለቱ ዓሊተና ውስጥ የህዝብ ስብሰባ ይካሄድ ነበር አሉ። ስብሰባውን የሚመሩና የሚያስተዳድሩም ኦና ገብራይ ነበሩ። ታዲያ! ሁለቱ ብልጦች እንጀራውን ሰርቀው መብላታቸው እንዳይበቃ፤ ይኸው እንጀራህን እንያ ስብሰባው መኸል ላይ የተቀመጡ ሽበታሙ ሰውየ ወሰዱት፤ እሳቸውም ኦና ገብራይ ይባላሉ ይሉታል። የዋሁ ተማሪም ወደ ስብሰባ ቦታው ይሄድና ኦና ገብራይ አጠገብ እንደደረሰ **"ኦና ገብራይ'ዮ ዓዱሙሲ ያከክ ይ'እንገራ ደሀያ"** ይላቸዋል። ወደ አማርኛ ሲተረጐም ኦና ገብራይ! ቅሌት እንዳይከተል እንጀራዬን ይመልሱ ማለት ነው። ኦና ገብራይም መለስ አርገው፤ "**<u>ኳባክ ዓዱሙሲ ማራዒና!</u>** " ሲተረጐም፤ አዬ ልጄ ቅሌቱ አልቀረም! አሉት ይባላል። እናም! ይህ አባባል የሐጎስ ዮሐንስ መጣጥፍ አለመተማመንና ጥርጣሬን ያጠናከረ እንጂ ያስወገደ እንዳልሆነ ለማሳየት የቀረበ ግሩም አባባል ነው።

በፈጠራ ውሸት ላይ የተመሠረተ የሐጎስ ዮሐንስ ወሬ ወይም ፅሑፍ ከመነሻው አለመተማመንን፤ ጥርጣሬየንና ቅራኔን የመፍጠርና የማስፋት እንጂ የማጥበብ ባሕሪ የተላበሰ አይደለም። በመሆኑም ቅራኔ እንዳይፈጠር በመስጋቴ ነው የሚሉት ኦና ገብራይ እንዳሉት ማበላሸት ያለባቸውን ካበላሱ በኋላ መሆኑን የተገነዘቡት አይመስልም። ቅራኔና ጥርጣሬን የሚፈጥር ተግባርማ ገና የፈጠራ ወሬ ማውራት ሲጀምሩ አካትተውታል። "ዝአኽለን ያ ጠሕነንስ ባዓለማርያም ይብላ" ሲተረጐም "የሚበቃትን ፈጭታ ባዓለማርያም ነው ትላለች" የሚለው የትግርኛ ምሳሌያዊ አነጋገር እዚህ ላይ መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል ነው።

የሐጎስ ዮሐንስ "….በብቃት፤ **በጭብጥ አስደግፌ ራሴን ለመግለጽ መቻል አለመቻሌን ትንሽ እጠራጠራለሁ።"** የሚል አስፍረው እንደነበረ በዚህ ፅሑፍ ክፍል ሁለት ለማሳየት ተሞክሮ ነበር። ይህንን ረስተውት ይመስላል፤ አሁን **"…ካለኝ ማወላወል የሚመነጭ ሳይሆን**፤……፣" ይላሉ። "ዋናው <u>የጥርጣሬ</u> ምክንያት…" ሲሉ አሁንም የሚጽፉት መጣጥፍ ይዘት ላይ አለመተማመናቸውን ያሳያል። እውነትን የጨበጠ ጥርጣሬ ሊኖረው አይችልም። ጥርጣሬ ካለ የተጨበጠ እውነት የለም ማለት ነው። በማስረጃ የተደገፈ የተጨበጠ ነገር በእጅ ካልተያዘ ደግሞ እንዲህ ዓይነት የሚፃፍ ነገር ከተራ አሉባልታና የስም ማጥፋት ዘመቻ ውጭ ተደርጎ ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም። ይህ ደግሞ ቀኑ ደርሶ ግልጥልጡ እስኪወጣ ድረስ በህዝብ ውስጥ አለመተማመንና ጥርጣሬ መፍጠሩ አይቀሬ ይሆናል። ሐጎስ ዮሐንስ በፅሑፋቸው ውስጥ በኢሮብ ህዝብ መካከልና በኢሮብ ህዝብና በሌሎች ወገኖች መካከል ጥርጣሬና አለመተማመን እንዳይፈጠር መስጋታቸውን ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ፤ እውነትን ፍርጥርጥ አድርጎ በማውጣት መረጃውን ለህዝብ ይፋ ማድረግ በህዝቦች መካከል ጥርጣሬና አለመተማመን ሊፈጥር የሚችልበት ሁኔታ ምንና እንዴት ብሎ ሊከሰት እንደሚችል አላብራሩም። በዚህ ፀሐፊ እምነት የሚፃፈው ነገር ተጨባጭና በማስረጃ የተደገፈ እስከሆነ ድረስ ጥርጣሬና አለመተማመንን ያስወግዳል እንጂ አይፈጥርም። ወንጀለኞች ተጋልጠው በሕግ ሲቀጡ ማንነታቸውና የፈጸሙት ወንጀል ተለይቶ ወጥቶ ለህዝብ ይፋ ይሆናል። ወንጀለኞቹ ተለይተው ስለሚወጡም የተፈጠረ ጥርጣሬና አለመተማመን ቢኖር ጉዳዩ በማስረጃ ተረጋግጦ ሕጋዊ እልባት ስለሚያገኝ በሕብረተ-ሰቡ ውስጥ የተፈጠረው አለመተማመንና ጥርጣሬ ተወግዶ መተማመን ይፈጠራል። በአፄ ኃይለስላሴ አገዛዝ ዘመን በአንድ አከባቢ የሆነ ወንጀል ተፈጽሞ ወንጀለኛው ሳይታወቅ ሲቀር "አውጻጽ" አውጫጪኝ (አፍራሳታ) በማድረግ ፖሊስ ወንጀል ተፈጸመበት የተባለ አከባቢ ነዋሪ ህዝብን በመሰብሰብ ወንጀለኛውን አውጡ በማለት ህዝብን ያሰቃይ እንደነበረ የሚታወቅ ነው። ያኔ ገና ወንጀለኛው ባለመታወቁ በህዝብ መካከል ጥርጣሬና አለመተማመን ይነሳ ነበር። አንዴ ወንጀለኛው ከተገኘ በኋላ ግን ያ ተከስቶ የነበረው የጥርጣሬ ድባብ ተገፎ ይወልቅና ሁሉም ወገኖች ከጥርጣሬ ነፃ ይወጣሉ፤ መተማመንም ይነግስ ነበር። ይህ

ተግባር ህዝብን በማያውቀው ነገር የማንገላታት ገጽታ የነበረው ቢሆንም ሐጎስ ዮሐንስ እንደሚሉት ጥርጣሬና አለመተማመንን ለመፍጠር ሳይሆን ሱደረግ የነበረው ወንጀለኛውን ለይቶ በማውጣት በነዋሪዎቹ መካከል የነበረውን ጥርጣሬና አለመተማመን ለማስወገድ ነበር። በዚህም፤ ሐጎስ ዮሐንስ እውነትን ባወጣ ህዝብ ከህዝብ ጋር ይጣላል የሚሉት መላምት ውድቅ እንደሆነ ለማሳየት ይቻላል። ስለሆነም ሐጎስ ዮሐንስ ያለአመክንዮ ያቀረቡት ምክንያትም እንበለው መከራከርያ ነጥብ ውኃ የሚቋጥር አይደለም። በመሆኑም፤ ችግሩ ያለው ሐጎስ ዮሐንስ አእምሮ ውስጥ ብቻ እንደሆነ ሊሠመርበት ይገባል።

ሐጎስ ዮሐንስ በመቀጠልም ከላይ በተጠቀሰው ገጽና ፓረግራፍ እንዲህ ይላሉ፤

> *"ሌላው የጥርጣሬና የማወላወሌ መሠረት የውንጀላው እውነተኚነት ላይ ካለኝ ጥርጣሬ የሚመነጭ ነው። እኔ ከዕድሜ በታች የሆኑ የኢሮብ ሕፃናትን መልምሎ <u>ከዛሬው ሻዓቢያ</u> ጎን በማሰለፍ የኢሮብ ወገኖቹን ለማስፈጀት የሚሠራ የኢሮብ ተወላጅ አለ ብዬ ለማመን ፈጽሞ አልችልም።"*

እዚህ ላይ የሐጎስ ዮሐንስ እምነትና ተግባር የተለያየ መንገድ ይዘው እንደሚጓዙ ቁልጭ ብሎ ይታያል። ውንጀላው እውነተኛ ይሁን አይሁን እንዳላረጋገጡ በራሳቸው አንደበት፤ በራሳቸው ብዕር ከመመስከር አልፈው፤ ይህንን ዓይነት ተግባር ሊፈጽም የሚችል የኢሮብ ሰው ሊኖር ይችላል የሚል እምነትም እንደሌላቸው በጽሑፋቸው ውስጥ ቁልጭ ብሎ ሰፍሯል። ያም ሆኖ፤ ይህንን ሁሉ ይሆናል ብለው ለማመን ቸግሮዋቸው የነበረና ጭብጥ ይኑረው አይኑረው ለማረጋገጥ አስቸግሯቸው የከረመውን እንቆቅልሽ ማን እንደፈታላቸው እዛው በመጀመርያው ገጽ አንደኛ ፓረግራፍ እንደሚከተለው በማለት ***አንባቢአቸውን ያበስራሉ።***

> *"መጨረሻ ግን የጠቅላይ ሚኒስትራችን አቶ መለስ ዜናዊ ቃላቶች <u>እንዳምን አስገድደውኛል</u>።" ይላሉ።*

በመሠረቱ ይህ ፀሐፊ አቶ መለስ ዜናዊ የሚናገሩት ሁሉ እውነትና እውነት ነው የሚል እምነት የለውም። ይህ እምነቱ በስሜት ተገፍቶ የመጣ ሳይሆን በተጨባጭ መረጃዎች ማስደገፍ የሚቻል ነው። አቶ መለስ ሻዓቢያ የኢትዮጵያን ግዛቶች በእብሪት ሲወር፤ "ሳናውቀው ተወረርን" ያሉት በዚህ ፀሐፊ ጆሮ ሹክ ብለው ሳይሆን ዓለም እንዲያውቀው በይፋ ለጋዘጠኞች ጭምር የተናገሩት ፀሐይ ላይ የዋለ ሃቅ ነው። ሻዓቢያ ሊወረን በዝግጅት ላይ እንደነበረ አስቀድመው ስለማወቃቸው ግን የመረጃውን ምንጭ ይህ ፀሐፊ "ሉዓላዊነታችን ይከበር" በሚል መጣጥፉ ውስጥ አካትቶት ስለሚገኝ፤ እዛ ውስጥ መመልከት ይቻላል። አቶ መለስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው የነበሩት አቶ ስዩም መስፍን የሄግ ውሳኔ ይፋ የሆነ ዕለት፤ "በጦር ሜዳ የተጎናጸፍነውን ድል በፍርድ ቤትም ደገምነው" በማለት ሉዓላዊ ግዛቶቻችን ለኛ ተወሰኑልን በማለት እልል ብለን እንድንጨፍር ሲጋብዙን፤ አቶ መለስ ለህዝብ የተላለፈው መረጃ ስሕተት አለበትና መታረም ይገበዋል ብለው ሲናገሩ አልሰማንም። አንባቢን ላለማሰልቸት እንጂ በጣም ብዙ ነገር መደርደርና መተንተን ይቻላል። ሆኖም ሐጎስ ዮሐንስ ሊያምኗቸው ከመረጡ መብታቸው ነው። እውነቱን ለመናገር ከማመንም አልፈው "ንገሠለይ ደአዬ" ብለው ተሰክሞዋቸው በሰለሞን ተካልኝ "ቅንድቡ" ዘፈን ቢደንሱ ይህ ፀሐፊን የሚገደው አይሆንም። በሰው ትከሻ! ምን አግብቶት! በተቃራኒውም ይህ መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል ብሎ ለመሞገት ዝግጁ ነው። ጥርያቸውን ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል ግን ነገሩን አገናዝበን ለመገምገም እንዲረዳን አቶ መለስ ዜናዊ፤ ሐጎስ ዮሐንስ ካቀረቡት ውንጀላ ጋር በተዛመደ ያሉት ነገር ካለ፤ መቼና የት ምን እንዳሉ ምንጭና መረጃውን

ሊያቀርቡልን ይገባ ነበር። ካልሆነ ግን አቶ መለስ ተናግረውታል ብለው ያቀረቡት ጥቅስ ውስጠ ሚስጢሩ እኔ የምናገረው እውነት ነውና እንዲሁ በጭፍን እመኑኝ የሚል እድምታ ነው ያለው። ይህ ደግሞ በዛሬው ዘመን የሚሆን አይደለም፤ አይታሰብምም።ስለሆነም፤ የሚተላለፉ መልእክቶች በመረጃ ካልተደገፉ ቆሻሻ ማጠራቀምያን ከመሙላት ያለፈ ፋይዳ አይኖራቸውም። እረ ባክህ! እመነኝ ተብሎ የሚታለፍበት ዘመን አብቅቷል። ዘመኑ መረጃዎችን ማቅረብ የሚጠይቅ ዘመን ነው። በጭብጥ ያልተደገፉ ወሬዎች በቡና ሰዓት ላይ ሲወሩ የደጋፊ ወይም የላኪን ልብ ሞቅ ሞቅ የማድረግ አቅም ቢኖራቸውም ዘላቂ ፋይዳ አይኖራቸውም።ትርፉም ትእዝብት ብቻ ሆኖ ይቀራል። ልበ ሙሉነትና በራስ የመተማመን ስሜትንም ያከስማል። አጥብቆ ጠያቂ ሲመጣም ለሀፍረት ይዳርጋል። ስለሆነም፤ አቶ መለስ ዜናዊ የተናገሯቸው፤ እርሳቸውን ለማሳመን የበቁ የኢሮብ ሕፃናትን ለሻዓቢያ የሚመለምሉ የኢሮብ ተወላጆች እንዳሉ የሚያሳዩ መረጃዎች እኛን አንባቢዎችዎንም ለማሳመን ይረዳ ይሆናልና አቶ መለስ ያቀረቡት ጭብጥ እንዲያቀርቡልን የግድ ይላል። ካልሆነ ግን ወሬው እንደ ተራ ፈጠራ የሚቆጠር ይሆናል።

በመቀጠልም፤ በመጀመርያ ገጽ ፓረግራፍ 1 ላይ

> ***"በመሆኑም እንደ ኢሮብ፤ እንደ አንድ በኢሮብነቱ የሚኮራ ወንድ፤ ትግራዋይና ኢትዮጵያዊ በእውነቱ እነዚህ ጥርጣሬዎቼን፤ ፍርሐቴንና ማወላወሌን አቁሜ ስሜቴን ለማንጸባረቅ ቆርጫለሁ። የኢሮብ ወገኖቼም የኔን አርአያ ተከትለው እንዲያደርጉ እጋብዛለሁ።" በማለት የሳቸውን ዱካ እንድንከተል ጥሪ ያቀርቡልናል።***

እዚህ ላይ የሐጎስ ዮሐንስ ቆራጥነትና ኵራት በአንዱም ሆነ በሌላ ምክንያት እውነትን ጠምዝዘው፤ የሌለውን እንዳለ አድርገው ለማየት ለሚፈልጉና ከበስተጀርባ ሆነው የሶስተኛ አካልን ፍላጎት ለማሳካት ለሚሯሯጡ ግለሰቦች ጊዜያዊ የሞቅሞቅ ስሜት ሊፈጥር ይችላል። ከዛ ያለፈ ትርጉም ይኖረዋል ብሎ መጠበቅ ግን ቅጥ ያጣ የዋህነት ይሆናል። የሆነ ሆኖ የሐጎስ ዮሐንስ ወንድነትና ቆራጥነት ማስረጃውን በማቅረብ ቢደገፍ ኖሮ እውነቱን ለመናገር ይህ ፀሐፊም እንደ ጀግናው ሊቆጥራቸው በቻለ ነበር። ለነጭ ውሸት ሲባል ቆራጥና ጀግና መሆን ግን አስፈላጊ ይሆናል ብሎ አያምንም። ዱካቸውን ለመከተል የቀረበው ጥሪን በሚመለከት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በስሜት ለሚነዱና በትግራይ ኦን ላይን (Tigraionline.com) ላይ በመጻፍ የተሳደበው ሰው ዓይነቶችን ልብ ሊማርክ ይችል ይሆናል። ደግነቱ በስሜት የሚነዳው ወገን በቁጥር ሲሰላ እዚህ ግባ የሚባል ካለመሆኑም በላይ ሰክኖ ነገሮችን የማየት ክህሎት ያላቸው ወገኖቻችን እጅጉን በርካታ ናቸው። ስለሆነም፤ ለመከተልም ላለመከተልም ጭብጥ ይጠይቃሉ። ያ ጭብጥ እንዳሁኑ አድበስብሶ በብልጣብልጥነት ለማለፍ ከተሞከረም ጥሪው ፋይዳ አይኖረው ማለት ብቻ ሳይሆን "ተንጋልለው ቢሸኑ..." እንደሚባለው ተመልሶ የባለቤቱን ጭንቅላት ያፈርጣል። የጊዜ ጉዳይ እንጂ ይህ እውን እንደሚሆንም ቅንጣት ታክል የሚያጠራጥር አይደለም። እዚህ ላይ "ሐቂ ፋትሊ ሓሞማካህ ሚያጊሪዕ" (የእውነት ክር ይቀጥናል እንጂ ፈጽሞ አይበጠስም) የሚለውን የኢሮብ ቢሂልን ማስተዋል ተገቢ ይሆናል።በመሆኑም፤ ጭብጥን ያልያዘ ዘገባ ተከትሎ ጥሪውን የሚቀበል ጤነኛ ሰው ይኖራል ብሎ መገመት የሚቻል አይሆንም።ስለዚህ እንድንከተላቸው ከልብ የሚፈልጉ ከሆነ ሐጎስ ዮሐንስ አለኝ የሚሉትን ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

ሐጎስ ዮሐንስ አሁንም፤ መጀመርያ ገጽ-1ኛ ፓረግራፍ

> ***"አገር ቤት ካለው የኢሮብ ህዝቤ የሰማሁት እውነት ከሆነ፤ እነዚህን ከዕድሜ በታች የሆኑትን ሕፃናት ለመታደግና በኢሮብ ህዝብ፤ በኢሮብ ህዝብና በመንግሥታቸው መካከል***

> ***በመቀጣጠል ላይ የሚገኘውን እሳተ-ነበልባል ለማጥፋት ያለኝን ሁሉ ብሰዋ ኩራት ይሰማኛል" በማለት ይቀጥላሉ።***

አገር ቤት ካለው የኢ.ሮብ ህዝብ "<u>የሰማሁት እውነት ከሆነ</u>" የሚለውን አገላለጽ አንባቢ ልብ ሊለው የሚገባ ነው። ሐጎስ ዮሐንስ በአንድ በኩል እውነቱ ተገልያልኛል፤ የኢ.ሮብ ሕፃናትን ለሻዓቢያ የሚቸበችቡ የኢ.ሮብ ተወላጆች እንዳሉ በማስረጃ አረጋግጫለሁ ይላሉ። በሌላ በኵል ደግሞ ህዝብ ነገረኝ ያሉትን "በጆሮአቸው የሰሙትን" ማለት ነው ጥያቄ ውስጥ ያስገባሉ። ሐጎስ ዮሐንስ በአንድ ፅሑፍ ውስጥ እርስ በርሱ የሚቃረን ሐሳብ እያራመዱ መሆኑ ግልጽ ነው። "ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ" ተብሎ የለ! ለራሳቸው ሲሆን ምንም ማስረጃ ሳያቀርቡ እንዲታመኑ ይማጸናሉ። ህዝብ የነገራቸውን ግን ይጠራጠራሉ። ሐጎስ አንድ ሚዛን ይኑርዎት። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ "ሰው በምንም ሆነ በምን ዘዴና መንገድ ራሱን ወይም አመለካከቱን ያቅርብ!፤ የሚነግርህ ነገር ሃቅ ነው። የሚሰማውና የሚያምነውም ይህንን ነው" ብለዋል በማለት ይጠቅሱዋቸዋል። ይህ ፀሐፊ የዚህ ጥቅስ እድምታን፤ ሐጎስ ዮሐንስ ሌላ ማብራሪያ ካልሰጡን በስተቀር፤ የማቀርበው ምን ይሁን ምን! እኔን እምኑኝ በማለት እንድናምናቸው እየተማጸኑ እንደሆነ አድርጎ ተመልክቶታል። ይሁን እንጂ በዚሁ ዓረፍተ-ነገር ውስጥ ራሳቸውን ሲቃረኑ ይታያል። ይኸውም "የኢ.ሮብ ህዝቤ ነገረኝ የሚሉትን **"የሰማሁት እውነት ከሆነ"** በማለት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ያስገባሉ። ፈረንጆች (double standard) ሁለት ሚዛን የሚሉት ይህን ነው። እርሳቸው ማስረጃ ሳያቀርቡ መታመን ካለባቸው፤ ህዝባቸው ያለቸውን ማመን ይጠበቅባቸው ነበር። እርሳቸው ህዝብ ነገረኝ የሚሉት ነገር ላይ ጥርጣሬ ካላቸው! እኛ እሳቸው ያሉንን ያለጥርጣሬ የምንቀበለው በምን መመሥፈርት ነው? ለነገሩ የጠቀሱት የአቶ መለስ ዓረፍተ ነገርም ቢሆን መርጣቹህ እመኑ አይልም። ቢሆንም፤ መቼና የት ከምን ሁኔታ ጋር አዛምደው እንደተናገሩት መገለጽ ነበረበት። ይሁንና እዚህ ላይ እንደ ዋና ቁምነገር ተደርጎ መወሰድ ያለበት ጉዳይ ቢኖር ህዝባችን የሌለውን ነገር እንደማይናገር ነው። ከተናገረ ደግሞ ለመናገር ያበቁት ጭብጦች አሉት ማለት ነው። ስለሆነም ከሐጎስ ዮሐንስ የሚጠበቀው ህዝብ እንደ ህዝብ የነገራቸውን ጥርጣሬ ውስጥ ማስገባት ሳይሆን፤ ከነገራቸው ህዝብ ማስረጃውን አሰባስበው አለኝ የሚሉት እውነት ይፋ ማድረግ ነው።

ከዚህ በመቀጠል ወደ "ኢ.ትዮ-ኤርትራ የድንበር ጦርነት" ያስገቡንና ስለአፍሪቃ ቀንድ ባጭሩም ቢሆን ይተነትናሉ። ሌላውን በመተው አንዱን አስፈላጊ ዓረፍተ-ነገር እንውሰድ።

*መጀመርያ ገጽ ሁለተኛ ፓረግራፍ ላይ፤*

> ***"....የኢ.ትዮ-ኤርትራ የድንበር ጦርነት ከተጀመረ ይኸው ከአንድ አሰርት ዓመታት በላይ ሆኖታል።ለአንድ በአፍሪቃ ቀንድ ለዘመናት በመካሄድ ላይ ያለውን ሁኔታና የሄጉን ውሽልሽል/ሙልጭልጭ ውሳኔን በጥሞናና በብልሃተኝነት ለሚከታተል ሰው፤ ይህ ህውከት በቀላሉና በጭር ጊዜ መፍትሔ ካገኙት የዚህ ጊዜ ህውከቶች አንዱ ይመስላል።"***

እዚህ ላይ ሐጎስ ዮሐንስ የኢ.ትዮ-ኤርትራ "የድንበር" ጦርነት ሲያወሱ የሄጉ ገላጋይ ፍርድቤት የሰጠውን ብይን "ውሽልሽሉን የሄግ ብይን" ወይም "ሙልጭልጩን የሄግ ውሳኔ" በሚል ሐረግ ያልፉታል። ከዛም አልፎ በቀላሉና ባጭር ጊዜ እንደተፈታ ችግር አድርገው አይተውታል። ለሳቸው የህዝባችንና ግዛታችን የሁለት ዓመት ስቃይ አጭርና ቀላል መሆኑ ነው። አመለካከታቸው ነው፤ ይህንን አመለካከትና ግምገማ መያዝም መብታቸው ነው። ይህ ፀሐፊ ግን ይህንን የሐጎስ ዮሐንስን አመለካከት አይጋራም፤ ብቻ ሳይሆን እጅጉን ይለያል። በራሳቸው ፅሑፍ ውስጥ የጠቀሱት የ70፣ 000 ሰው ሕይወት ቀላል ነው አይልም። ለሁለት ዓመታት የተበሳበሰው ህዝባችንና የወደመው

ንብረት ያንገበግቧል። እንዲህ በአንድ ዐቅሙን በማያውቅ እብሪተኛ መወረርም ያበግናል። ይህንን አስመልክቶ ብዙ ለማለት የሚቻል ቢሆንም፤ ይህንን አሳምሮ ለሚያውቀው ህዝባችን ለመግለጽ መሞከር ቀባሪን እንደማርዳት የሚቆጠር ስለሚሆን በዚሁ እንለፈውና፤ "ውሽልሽል" ወደአሉት የሄግ ውሳኔ እናምራ። ሐጎስ ዮሐንስ ልብ ያላሉት ነገር ቢኖር "ውሽልሽል" ወይም "ሙልጭልጭ" የሆነው የሄጉ ውሳኔ ሳይሆን የሄግ ውሳኔ እንዲወሰን ያመቻቸውና የሄግ ውሳኔ የሚወስኑ የግልግል ፍርድ ቤት ዳኞችን ያቋቋመው እነ አቶ መለስ ዜናዊ ወደውና ፈቅደው ያፀደቁትና የፈረሙት የአልጀርስ ውል መሆኑን ነው። የሄግ ብይን የአልጀርስ ስምምነት ውጤት መሆኑ መዘንጋት የሌለበት ነጥብ ነው። በመሆኑም፤ የሄጉን ብይን እ.ኤ.አ ሰኔ 18 ቀን 2000 ዓ.ም በኢትዮጵያ ገዢዎችና በ"ሀገረ" ኤርትራ በተፈረመው ባለ 6 አንቀጽ የአልጀርስ ስምምነት የተወለደ የግልግል ፍርድ ቤት እንጂ የራሱ የሆነ ህልውና ያልነበረውና የሌለው መሆኑ ሊዘነጋ ባልተገባ ነበር። ስለሆነም፤ በአንዱም ሆነ በሌላ ምክንያት የወቅቱን አገዛዝ በመውደዳችን ወይም ባለመውደዳችን ነባራዊ ሁኔታው ሊቀየር ፈጽሞ አይችልም። በአልጀርስ ስምምነት መሠረት በሄግ የተሰየመው የግልግል ፍርድቤት የሰጠው ብይን ብሔራዊ ጥቅማችንን የሚጎዳ በመሆኑ እኛ ባንቀበለውም፤ የአልጀርሱን ውል ተቀብሎ የሄግ ውሳኔን "ውሽልሽል" ወይም "ሙልጭልጭ" ነው ብሎ መናገር ሚዛን የሚደፋ ክርክር አይደለም። የሄግ ብይን የአልጀርሱ ስምምነት ውጤት መሆኑን ለመረዳት መቻል እምብዛም የሚያዳግት መሆን አልነበረበትም። ሻዓቢያ፤ መጀመርያ በሕወሓት/ኢህአዴግ ይሁንታ አገራችንን በሁለገብ መልኩ እየበዘበዘ ኤርትራን ለማልማት ይዘባነንብን እንደነበረ ለማሳየት ብዙ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል። ይህ ራሱ የአገር ሀብት ወረራ እንደነበረ የምንዘነጋው አይደለም። ቀጥሎ የትግራይ ገበሬ የሕወሓት መሪዎች አገርን የማስበዝበዝ ተግባር አልዋጥ ብሎት ወደ ኤርትራ የሚጋዘውን የኢትዮጵያ ንብረት አላሳልፍም ሲል ሻዓቢያ በጀብደኝነት ተነሳስቶ አገራችንን ወረረ። በልዑላዊ ግዛቶቻችን በቆየባቸው ሁለት ዓመታት ውስጥ የነበሩን አንስተኛ በሕብረተ-ሰቡና ቤተክርስትያን የተሠሩ መሠረተ-ልማቶችን አፈራርሷል። ቤተ መቅደሶቻችንን የጦር መጣርያ ማከማቻ አድርጓቸዋል። ከአንድ መቶ በላይ ወገኖቻችንን አግቶ ወስዶ እስከ ዛሬ መድረሻቸው አልታወቀም። የሚጠይቅላቸው መንግሥትም የለም። ከሁለት ዓመት በኋላ አይከፈል ዕዳ ተከፍሎ ሻዓቢያ ከግዛታችን ወጥቷል። ምስጋና ለጀግናው አልበገሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን። ይሁንና የተከፈተብን ወረራ በማያዳግም መልኩ እንዳይገባደድ አቶ መለስ አሽመድምደውታል። በዚህም ሻዓቢያ ዛሬም ለህዝባችን ሰላም አደጋ ሆኖ በመቀጠል ላይ ይገኛል። ይህም አልበቃ ብሎ በጦር ሜዳ የተገኘውን ድል አቶ መለስ አልጀርስ ወስደው ለሻዓቢያ አስረክበው ተመልሷል። ምን ማድረግ ነበረባቸው የሚሉ አንባቢያን ሊኖሩ ይችላሉ። መደረግ የነበረበትማ! በጦር ሜዳ የተገኘውን ድል ማስጠበቅ ነው። አገርህን የወረረ ወራሪ ከወረራቸው ሉዓለዊ ግዛቶች ካባረርክ በኋላ ሉዓላዊ መሬትህን ለድርድር አታቀርብለትም። ይልቁንስ ሻዓቢያ መፈረም የነበረበት ግዴታ፤ የተሸናፊ ግዴታን መሆን ነበረበት። ይኸውም፤ በዕብሪት የከፈትክብንን ጦርነት በድል አገባድደነዋል። አሁን ያለህ አማራጭ የዘረፍከው ንብረታችንን ለመመለስ፤ ያገትካቸው ወገኖቻችንን አሁኑኑ ነፃ ለመልቀቅ፤ የወረርካቸው ሉዓላዊ የኢትዮጵያ ግዛቶችን እንደገና ስማቸውንም እንኳ ላለማንሳት፤ የኢትዮጵያን የባህር በር የማግኘት መብት እውቅና ለመስጠት፤ ከእንግዲህ ኢትዮጵያን ላለመተንኮስ፤ ላደረስከው ጉዳት ሙሉ ካሳ ለመክፈል ተስማምቻለሁ ብለህ መፈረም ነው ተብሎ ሊነገረው በተገባ ነበር። ይህንን ግዴታ መፈረም የነበረበትም ከአሸናፊ ጋር እኩል ሆኖ ሳይሆን ተሸናፊነቱን አምኖና ተቀብሎ እንደ ውሻ አንገቱ ላይ በሰንሰለት ታሰሮ፤ አልጀርስ ላይ ሳይሆን፤ እዛው ሠራዊታችን በተቆጣጠራቸው የኤርተራ ክፍለ ሀገር ውስጥ ሰንዓፈ ወይም አቁርደት ላይ መሆን ነበረበት። ያ ሳይሆን ቀርቶ አቶ መለስ ዜናዊ አልጀርስ ድረስ በመሄድ ተሸናፊ አሸናፊ ሆኖ የሚወጣበት ውል ተፈራርመው ተመልሷል። የሄግ ውሳኔ የሚፈልቀው

እንግዲህ ከዚህ ውል ነው። በመሆኑም የአልጀርሱን ውል ተቀብሎ የሄግን ውሳኔ "ውሽልሽል" ብሎ መጥራት አድርባይነት የተቀላቀለበት አባባል ነው። ለሐጎስ ዮሐንስና መሰሎቻቸው አንድ ጥሪ ማቅረብ ተገቢ ይሆናል። ይኸውም! ሁላችን በጋራ ሁነን የአልጀርሱን ውል እንዲሰረዝ መጥራትና መሥራት ነው። የሉዓላዊነታችን መከበር መሠረታዊና ዋስትና የአልጀርሱን ውል ውድቅ ማድረግ ብቻ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

በሚቀጥለው እስከምንገናኝ በሰላም ያቆየን!!!

ይቀጥላል……

የካቲት 20 ቀን 2011 ዓ.ም.ፈ